17- ለምድር ብርሃን እንዲሰጡ እነዚህን በሰማይ ጠፈር አኖራቸው።

18- ይኸውም በቀንና በሌሊት እንዲሠለጥኑ፣ እና ብርሃንን ከጨለማ እንዲለዩ ነው። እግዚአብሔርም ይህ መልካም እንደ ሆነ አየ።

19- መሸ ነጋም አራተኛ ቀን።

- በአራተኛው ቀን እግዚአብሔር ፀሐይን ጨረቃን እና ክዋክብትን ፈጠረ።

- እግዚአብሔር ፀሐይን ጨረቃንና ከዋክብትን የፈጠራቸው እንዴት ነው?

- እግዚአብሔር ፀሐይን ጨረቃን እና ከዋክብትን የፈጠረው በመናገር ብቻ ነው።



## ትምህርት 6

1. መጀመሪያው ምንድን ነው?

ሀ- መጀመሪያው ከረጅም ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች የፈጠረበት ጊዜ ነው።

2. በመጀመሪያው በዚህ ዓለም የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ የፈጠረው ማን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ነው።

3. እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከመፍጠሩ በፊት በዚህ ዓለም ውስጥ ምን ነበረ?

ሀ- ምንም ነገር አልነበረም።

4. በዚህ ዓለም ምንም ነገር ካልኖረ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከምን ፈጠረ?

ሀ- ከምንም።

5. ታዲያ እግዚአብሔር ዓለምን እንዴት ፈጠረ?

ሀ- እግዚአብሔር ዓለምን ከምንም ፈጠረ።

6. እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከምንም እንዴት መፍጠር ቻለ?

ሀ- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ በመሆኑ።

ለ- የእግዚአብሔር ኃይል ማብቂያ የሌለው በመሆኑ።

ሐ- የእግዚአብሔር ኃይል ዘላለማዊ በመሆኑ።

7. የእግዚአብሔር ኃይል ወሰን አለው?

ሀ- የለውም።

8. ሰይጣን ወይም አጋንንቱ ወይም ሰዎች ከእግዚአብሔር የበለጠ ኃይል አላቸው?

ሀ- የላቸውም።

9. እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንዴት መፍጠር እንዳለበት ያስተማረው አለ?

ሀ- የለም።

10. እግዚአብሔርን ማንም ያላስተማረው ለምንድን ነው?

ሀ- በመጀመሪያ እግዚአብሔርን የሚያስተምረው ማንም በዚያ አልነበረም።

ለ- በተጨማሪም እግዚአብሔርን ማንም ያስተምረው ዘንድ አያስፈልገውም።

11. የእግዚአብሔር ጥበብ ወሰን አለውን?

ሀ- የለውም።

12. ከእግዚአብሔር የበለጠ ጠቢብ አለ?

ሀ- የለም።

- በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ከመፍጠሩ በፊት ምድር ምን ትመስል እንደነበረች እስቲ እናንብብ።

ዘፍጥረት 1፡1-2ሀ

1- በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ።

2- ምድርም ቅርጽ የለሽና ባዶ ነበረች። የምድርን ጥልቅ ስፍራ ሁሉ ጨለማ ውጦት ነበር።»



- እግዚአብሔር ተክሎችንና ዛፎችን ሁሉ የፈጠረው ለማን ነው?

- እግዚአብሔር የፈጠራቸው ለእኛ ለሰዎች ነው።

- እግዚአብሔር ተክሎችንና ዛፎችን ለምን ፈጠራቸው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር እኛን እጅግ ስለሚወደን ነው።

- ዛፎች ባይኖሩ ኖሮ ቤት መሥራት ትችላላችሁን?

- አዎን አትችሉም።

- እግዚአብሔር ስለሚወደን ተክሎችን የፈጠረው ለእኛ ነው።

- እህል ባይኖር ምን ትበላላችሁ?

- አስቸጋሪ ነው።

- እግዚአብሔር ስለሚወደን እህልን የፈጠረው ለእኛ ነው።

- እግዚአብሔር በአራተኛው ቀን ምንን ፈጠረ?

ዘፍጥረት 1፡16-19

16- እግዚአብሔር፣ ለምድር ብርሃን ይሰጡ ዘንድ ሁለት ታላላቅ ብርሃናት አደረገ፤ ታላቁ ብርሃን በቀን እንዲሠለጥን፣ ታናሹ ብርሃን በሌሊት እንዲሠለጥን አደረገ። እንዲሁም ከዋክብትን አደረገ።

12- ምድር ዕፀዋትን፣ እንደየወገናቸው ዘር የሚሰጡ ተክሎችንና በውስጣቸው ዘር ያለባቸው ፍሬ የሚየፈሩትን ዛፎች በየወገኑ አበቀለች። እግዚአብሔርም ይህ መልካም እንደሆነ አየ።

13- መሸ፣ ነጋም፤ ሦስተኛ ቀን።

- በሦስተኛው ቀን እግዚአብሔር ተክሎችንና ዛፎችንም ፈጠረ።

- እግዚአብሔር ተክሎችንና ዛፎችን የፈጠረው እንዴት ነው?

- እግዚአብሔር ተክሎችንና ዛፎችን ሁሉ የፈጠረው በመናገር ብቻ ነው።

- ተክሎችንና ዛፎችን መፍጠር ለእግዚአብሔር አስቸጋሪ ነበር?

- አልነበረም።

- ለምን?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔርን የሚያቅተው ምንም ነገር የለም።

- እግዚአብሔር ስንት ዓይነት የተለያዩ ተክሎችንና ዛፎችን ፈጠረ?

- እጅግ ብዙ ናቸው።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ተክሎችና ዛፎች ለምን ፈጠረ?

- እግዚአብሔር ለመኖር ተክሎችና ዛፎች ያስፈልጉታል?

- አያስፈልጉትም።



- እግዚአብሔር ከመፍጠሩ በፊት ዓለም ምን ይመስል ነበር?

- በመጀመሪያ ብርሃን አልነበረም።

- በመጀመሪያ ጨለማ ምድርን ሁሉ ሸፍኖት ነበር።

- በቀን የፀሐይ ብርሃን ባይኖር ትደስታላችሁ?

- አንደሰትም።

- በሌሊት የጨረቃ ብርሃን ባይኖር ትደስታላችሁ?

- አንደሰትም።

- በምድር ላይ ብርሃን ከሌለ አስፈሪ አይሆንም?

- ይሆናል።

- እርስ በርሳችሁ መተያየት አትችሉም።

- እህላችሁን ለመዝራት ብትፈልጉ አይታያችሁም።

- ቤታችሁን መሥራት ብትፈልጉ አይታያችሁም።

- በመጀመሪያ ብርሃን አልነበረም።

- በመጀመሪያ ደረቅ ምድርም አልነበረም።

- በመጀመሪያ ውኃ ምድርን ሁሉ ሸፍኖ ነበር።

ዘፍጥረት 1፡2ለ

2- የምድርን ጥልቅ ስፍራ ሁሉ ጨለማ ውጦት ነበር፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሆች ላይ ያረብብ ነበር።

- በመጀመሪያ በምድር ላይ ሕይወት አልነበረም።

- ነገር ግን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በዚያ ነበረ።

- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም ነገር ለመፍጠር ይጠባበቅ ነበር።

- አንድ እግዚአብሔር ብቻ እንዳለና አንድ እግዚአብሔር ሦስት አካላት እንዳሉት ታስታውሳላችሁ።

- እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ነገር በአንድነት ፈጠሩ።

- በመጀመሪያ እግዚአብሔር በአንደኛው ቀን ምንን ፈጠረ?

ዘፍጥረት 1፡3

3- ከዚያም እግዚአብሔር «ብርሃን ይሁን» አለ። ብርሃንም ሆነ።

- በአንደኛው ቀን እግዚአብሔር ብርሃንን ፈጠረ።

- እግዚአብሔር ብርሃንን በአንደኛው ቀን የፈጠረው እንዴት ነበር?

- እግዚአብሔር ብርሃንን የፈጠረው በመናገር ብቻ ነበር።



10- እግዚአብሔር ደረቁን ምድር፣ «የብስ»፤ በአንድነት የተሰባሰበውን ውኃ «ባሕር» ብሎ ጠራው። እግዚአብሔር ይህ መልካም እንደ ሆነ አየ።

- በሦስተኛው ቀን እግዚአብሔር ደረቅ ምድር ፈጠረ።

- ደረቅ ምድር ይታይ ዘንድ ውኃው ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ ያዘዘው ማን ነው?

- እግዚአብሔር ነው።

- እግዚአብሔር ውኃው ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ ማዘዝ የቻለውና ወኃውም የታዘዘው በምን ምክንያት ነው?

- ምክንያቱም ውሃን የፈጠረው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

- አንድ ሰው ወንዝ አጠገብ ሲደርስ፥ መሻገር እንዲችል ውኃው እንዲያፈገፍግለት ማዘዝ ይችላል?

- አይችልም።

- እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን ሌላ ምንን ፈጠረ?

ዘፍጥረት 1፡11-13

11- «እግዚአብሔር ምድር ዕፅዋትንም፣ እንደየወገናቸው ዘር የሚሰጡ ተክሎችንና በምድር ላይ ዘር ያዘሉ ፍሬ የሚያፈሩ ዛፎችን እንደየወገናቸው ታብቀል» አለ። እንዳለውም ሆነ።

- በሁለተኛው ቀን እግዚአብሔር ጠፈርን (ሰማይን) ፈጠረ።

- እግዚአብሔር በሁለተኛው ቀን ጠፈርን (ሰማይን) የፈጠረው እንዴት ነበር?

- እግዚአብሔር ጠፈርን (ሰማይን) የፈጠረው በመናገር ብቻ ነበር።
- ጠፈርን መፍጠር ለእግዚአብሔር አስቸጋሪ ነበር?

- አልነበረም።

- ለምን?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር የማይችለው ምንም ነገር የለም።

- እግዚአብሔር መሬትን የሸፈነውን ውኃ የለየው እንዴት ነበር?

- እግዚአብሔር ከፊሉን ውኃ ከጠፈር በላይ አኖረው።

- እግዚአብሔር ቀሪውን ውኃ በምድር ላይ ተወው።

- እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን ምንን ፈጠረ?

ዘፍጥረት 1፡9-10

9- ከዚያም እግዚአብሔር «ከሰማይ በታች ያለው ውኃ በአንድ
ስፍራ ይከማች፤ ደረቁ ምድር ይገለጥ» አለ፤ እንዳለውም ሆነ።



- ብርሃንን በመናገር ብቻ መፍጠር የሚችል ከእግዚአብሔር ሌላ አለ?

- የለም።

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡

- አንድ ምሽት ምንም ብርሃን በሌለበት ጥቅጥቅ ያለ ደን ውስጥ ናችሁ እንበል።

- በዚያ የጨረቃም ሆነ የከዋክብት ብርሃን የለም።

- ድቅድቅ ጨለማ ነው፤ ስለሆነም ምንም ነገር ማየት አትችሉም።

- «ብርሃን ይሁን!» ብትሉ ብርሃን ይሆናል?

- አይሆንም።

- ነገር ግን እግዚአብሔር ሲናገር ብርሃን ተፈጠረ።

- ብርሃንን መፍጠር እንደሚቻል እግዚአብሔር እንዴት አወቀ?

- እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያውቃል።

- እግዚአብሔር የማያውቀው ምንም ነገር የለም።

- ብርሃንን መፍጠር ለእግዚአብሔር አስቸጋሪ ነበር?
- አልነበረም።

- ለምን?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔርን የሚያቅተው ምንም ነገር የለም።

- እግዚአብሔር ስለ ፈጠረው ብርሃን ምን አሰበ?

### ዘፍጥረት 1፡4ሀ

4- እግዚአብሔርም ብርሃኑ መልካም እንደ ሆነ አየ።

- እግዚአብሔር የፈጠረው ብርሃን መልካም ነበረ።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍጹም ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር የሚሠራው ነገር ሁሉ ፍጹም ነው።

- ሰዎች ቤቶችን ይሠራሉ፤ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ጣሪያቸው ያፈሳል።

- ሴቶች ማሠሮዎችን ይሠራሉ፤ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ማሠሮዎቹ ይሰበራሉ።

- ነገር ግን እግዚአብሔር የሠራቸው ነገሮች ሁሉ ፍጹም ነበሩ።

- ለምን?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍጹም ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር ብርሃንን ከፈጠረ በኋላ ምን አደረገ?



### ዘፍጥረት 1፡4ለ-5

4- እግዚአብሔር ብርሃንን ከጨለማ ለየ።

5- እግዚአብሔርም ብርሃኑን «ቀን»፣ ጨለማውን «ሌሊት» ብሎ ጠራው መሸ ነጋም፤ የመጀመሪያው ቀን።

- እግዚአብሔር ብርሃንን በፈጠረበት ጊዜ ሁሉንም ጨለማ አላስወገደውም።

- እግዚአብሔር ከፊሉን ጨለማ የምሽት ጊዜ እንዲሆን ተወው።

- እግዚአብሔር ምንም ጨለማ ባያስቀር ኖሮ ምን ይሆን ነበር?

- እኛ መተኛት አንችልም ነበር።

- እግዚአብሔር ተኝተን እንድናርፍ ከፊሉን ጨለማ ተወው።

- እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር ሁሉ ፍጹም ነው።

- እግዚአብሔር በሁለተኛው ቀን ምንን ፈጠረ?

### ዘፍጥረት 1፡6-8

6- እግዚአብሔር «ውኃን ከውኃ የሚለይ ጠፈር በውሆች መካከል ይሁን» አለ።

7- ስለዚህ እግዚአብሔር ጠፈር አድርጎ ከጠፈሩ በላይና ከጠፈሩ በታች ያለውን ውሃ ለየ፤ እንዳለውም ሆነ።

8- እግዚአብሔር ጠፈረን፣ «ሰማይ» ብሎ ጠራው። መሸ፣ ነጋም፤ ሁለተኛ ቀን።